“ የሥጋ ውስጥ ነፍስ ”

መዘክር

የዚች ቁንፅል ግጥም በረከትነት እርስ በርስ የሚኖሩና የሚቃረኑ ያስተሳሰብ ግጭቶች በሥፈኑበት ህብረተሰብ ውስጥ የሚኖር አስተዋይ ዜጋ ለሚደርስበት የመንፈስ ጭንቀትና ሽብር ማፅናኛ ትሆነው ዘንድ የተበረከተች ናት።

የግጥሙ ሠራዊት

አዝማች

“ - - - ልዩ ሀይል አግኝቶህ እስክታገኝ ዋጋ፣

በነፍስ አትጫወት ተው ሥጋ ተው ሥጋ - - - ”

/የሥጋ ውስጥ ነፍስ/

1960 ዓ/ም

“ የሥጋ ውስጥ ነፍስ ”

የዱዳሌብ አፈር፣

የአዜቡ አየር፣

የኮሬቡ እሳት

የናጊቡ ውሃ ባራት ተዋህዶ በአንድ ሰውነት

ሰውን ሰው አድርገው ሊባል ቅድመ ፍጥረት

የሚጸረሩ ቅይር ባህሪያት

የሚቃረኑት ልውጥ ኑባሬያት

መሬትና ውሃ ነፋስና እሳት

ሆነው ተዋህዶ በፍፁም አንድነት

ሥጋና ነፍስ ሆነው

ተብለው ልዩ ሠው፤

ግዝፈት ከርቀት ጋር

አካልና መንፈስ በሥምረታዊ ህብር

ተባብረው በፍቅር

በልዩ ተአምር፤

እሳትን በውእየት

በዚያ ብሩህነት በቁር ይቡስነት

ከነፋስ ከውሃ እንዲሁም ከመሬት

ያለውድ በግድ አዋህዶ ይዞት፤

ነፍሱን በውዕየት

በዚያ ቁራዊነት በዚያ ፅሉምነት

ከውሃ ከመሬት እንዲሁም ከእሳት

ያለውድ በግድ አቆራኝቶ ይዞት፤

ውሃውንም ደግሞ በዚያ ርጡብነት

በብሩህነትና በሃያል ቁርነት

ከነፋስ ከእሳት እንዲሁም ከመሬት

ያለውድ በግድ አወሳስቦ ይዞት

ለያንዳንዱ ፀባይ ሶስት ሶስት ግብሮች ሰጥቶት፤

ሰው ተባለ አዳም

በሥጋና ባጥንት እንደዚሁም በደም

ታሸነ አካሉ ባዶናይ ማህተም

ነፍስም በበኩሏ በሶስት ባህሪያት

ነባቢት ልባዊት እንዲሁም ህያዊት

የሚል ድንጋጌ ታወጀባት ሥርአት

በሊህ ተከርችማ ተቸንክራ አለች ውስጣዊቷ ህይወት።

ባለባት ግዴታ

ያላንዳች ቅሬታ፤

በነባቢት ግብሯ ለሰውናት አንደበት

በለባዊት ግብሯ ሀሣብ ናት መሠረት

በህያዊነቷም ህያው ናት ለህይወት።

በሷ ልባዊነት ህሊና ያስባል

በሷ ህያውነት በድኑ ያ ሥጋ ሊንቀሳቀስ ችሏል።

ይህ ነው ጥበባችን ሀይማኖት ያፈራው

ስለ ሥጋና ነፍስ ባህላችን የሚያውቀው።

ባዲሱ ትምህርት በቅይሩ ጥበብ በመንፈስ ጎዳና

በዘመናይ እውቀት ሁኔታው ሲጠና

ያለው አስተሳሰብ ያለው ፍልስፍና

ከዚህም ጋር ባይሄድ አላቸው ዝምድና

“ . . . ሃይማኖት ከሳይንስ

ግዝፈትና መንፈስ

እሳትና ውሃ

ውስኪና ወተት።

ፍቅርና ጥላቻ

ፍቺና ጋብቻ

ተረትና ታሪክ

ህይወትና ተውሳክ፤

ተመሳሳይ ማግኔት

አይጥና ድመት።

ቡራኬና መርገም

ሽብርና ሰላም . . . ”

ናቸው ብለውናል ተጻራሪ ሀይሎች

ቅራኔ የወጣቸው ሁለት አንድነቶች።

በትርጉም በቃላት ብያኔያቸው ሲፈስ

አዲሱ ዘይቤ ይዟል ይህን መንፈስ።

አካል ነው ጥርቅም

የሚሊዮን ሴሎች ኒዩክለስና አቶም።

ሕዋስ ነፍስ ሴል

እንደሆነ ታውቋል

አዕላፍ ኬሚካል

በሌላኛው ልሣን “ ማተር ” ብለውታል።

ማተር በበኩሉ ምንነቱ ሲታይ

ንጥረ ባህርዩ ሲመረመርና ሲጠና በተለይ

ቁጥሩ አልፏል አሉ ከመቶ አስራ በላይ።

ልዩ ልዩዎቹ ያካል ኬሚካሎች

እርስ በርስ ሲብላሉ ይሆናሉ መሰራች

የመንፈስ የስትንፋስ የሀሣብ የስሜት እንዲሁም የሌሎች

ያካል አንቀሳቃሽ ብልቶች ነቅናቂ ሞተራዊ ሃይሎች።

በማተር ሥጋ ውስጥ መንፈስ እንዲፈጠር

ዋናው ኮረንቲ ነው የነፍስነት ምስጢር።

ለፅንሰት ሀሣብ አረቦን የሚሆን

ኔጋቲቭ ፖዘቲቭ ኮረንቲዎች አሉን

በሴሎቻችን ውስጥ የሚወክል ነፍስን

በአካል ባህር ውስጥ ምግብ ደም ሲሞላ

ግድቡ ልባችን ባለው ልዩ ሞተር ኬሚካል ሲያብላላ

ያንቀሳቅሰዋል በልብ ያለውን ሻፍት

በደም ጋን አውታሮች መንፈስን ለመስጠት

በደም ውስጥ ያሉቱ የኮረንቲ ኃይሎች

መሆናቸው ታውቋል የአካል አዛዦች

ተዘርግቶ ያለው ያካላችን አስራው

ያሰራጫል መኔፈስ ለእያንዳንዱ ብልት እንደሚያስፈልገው።

ያካልና የነፍስ ያሠራር ምስጥሩ

ይህ ነው ብለውናል ሳይበዛ ባጭሩ

ሳይንሱ ሲጨመቅ ያናቶሚ ግብሩ።

በሳይንስም ሆነ ወይም በሃይማኖት

ስለ አካል ያለውን ደረቁን እውነት

ሊኖር የሚችለው ዋህድ ፍልስፍና

ርቃት በግዝፈት አካል በልቦና

ሁለት አይነት በአንድ አንድ አይነት በሁለት

ሥጋና ነፍስ ናቸው የሠው ባህርያት

አበው እንዳቆዩን ነቢያት ሊቃውንት

የጥንቱ ሃዋርያ የዛሬት ሳይንቲስት።

ሊቃውንተ-ሥጋ ወሊቃውንተ ነፍስ

ሳይካትሪውም ሆነ ሌላው ሳይኮሎጂስት ስብከቱን ቢያናፍስ

ሐቁ ይኸው ብቻ እንደሆነ ታውቋል የሰው ፍጡር መንፈስ።

ስለዚሁ ጉዳይ የኔም አስተያየት

እንዲሆን አምናለሁ በሁለት አንድነት በአንድ ሁለትነት

መንፈስና አካል ወይም ሥጋና ነፍስ የሰው ልጅ ሰውነት

ተቀባይ ባገኘው በፍልስፍናና በሃይማኖት ትምህርት

ከዚህ ሁሉ ይልቅ እኔን ቀልብ ያሣጣኝ

ፍልስፍናው ሳይሆን ግራዬን ያጋባኝ

የዚያ የሥጋ ነው ያመፀኛው ጨካኝ

የሚውልባት ግፍ የሚያሣያት በደል ያቺን የዋሂቴ ነፍስ፣ ደስታን ስትመኝ

ጥገኛው በመሆን በውስጡ ስትኖር እሱን ብላ ሙጥኝ።

ሥጋ ባለው ምኞት በተፈጥሮ ህጉ

ቢበላ ቢጠጣ ቢለበስ ቢሰስን ነው አሉ ማዕረጉ።

ነፍስ ግን በግሏ ያላት ልዩ ህይወት

ፈፅሞ አይደለም መብላት ወይ መጠጣት

እሷን እንዲህ ያለው ከቶም አይነካካት።

በሥጋ እንሰሳነት በነፍስ መልአክነት

ባህርይ ሥጋዊ ባህርይ ነፍሳዊ ባንድ ሰው ሰውነት

ሁለቱ ባንድ አካል በአንድ ሁለትነት

ተፃራሪ ሃይላት ቅራኔያዊ ጉልበት

አዳሪና ማህደር ተለያይቶ ውህደት

ረቂቁ መንፈስ ከስጋዊ ግዝፈት

ነው አሉ ሥራቱ ነጠላ ህላዊ መለኮት ወትስብእት።

ነፍስ ናት ነባቢት ነፍስ ናት ለባዊት ነፍስ ናት ህያዊት

የመለኮት አምሳል ያማኑኤል ቅንጣት ብናኝ የፀባኦት

ተናጋሪ አዋቂ ነዋሪ ዘለአለም ብልየት የሌለባት

ከታች ወርዳ ካዘቅት

እመቀ እመቃት

ከላይ ወጥታ ካናት

ከኪሩብ አርያም ካዮረ አዮራት

የመራቀቅ ቅብዓት የማሠብ ተውህቦ የመለፈስፈስ ፀጋ ካምላክ የተሠጣት

የትስብእት መገበዝ ምንም ያልበገራት

ከውህደት በስተቀር ዝምድና የሌላት

ሥጋ ከምንለው ከሰው ልጅ ሠውነት

የመንፈስ ባለቤት ነፍስ ናት ነፍስ ናት።

ጠባይዋ ይህ ሳይሆን የባይተዋሯ ነፍስ

ትቀጠቀጣለች ዘወትር ጧት ማታ በዚያ ሥጋ ደንደስ

ያንን ፍላጎቱን አረካለሁ ብሎ እንዲያ ሲልከሰከስ

ሲበላ ሲጠጣ ለከርሱ ሲያጋብስ

እንደበደላት ነው በሚያስከትለው ጦስ።

ሳይስማማው ቀርቶ የበላው የጠጣው

ጨጓራውን ሆነ አንጀቱን ሲቆርጠው

ሲወጋው ሲነፋው አለመጠን ሲያመው

የበሽታው ስቃይ ይበልጥ የሚያጠቃው

አካል ሥጋን ሳይሆን ያቺን ባይተዋር ነፍስ ደካማይቱን ነው።

በሱ ውስጥ ሆና ሥቃይ የምትጋት

በሱ ስልቻነት ታምቃ ታፍና ጭንቀት የተጫናት

በድፍን ጨለማ መከራን የሚያሳይ ሆኖባት እስር ቤት

ባርነት ብቻ እንጅ የሌለው ነጻነት

ፍርድም ሆነ ከብረት የማይገኝበት

መብት-አልባ የሆነ የተዳፈነ ቤት

በርግጥ ተጐድታለች ያች ነፍስ የዋሂት።

ያ ሥጋ ጎንትሎ ጨቃቁሶና ለክፎ በሚያስከትለው ጦስ

እንደበደላት ነው ነፍስን ታህል ፀጋ ያምላክ ፍንጣቂ

የመለኮት ብናኝ ደገኛዋን መንፈስ

ሥጋ ሲልከሰከስ ሲቃርም ሲሰስን መከራ ቢያገኘው

በግብዝነቱ አንዳች እከል ገጥሞት ሥቃይ በያሳድደው

ለደም ለአጥንቱ እንዲያ ሲንጦዘጦዝ እንዲያ ሲንሰፈሰፍ

እንቅፋት ሲያነጉደው

ራሱ ብቻውን ምናለበት ነበር ችግሩን ቢችለው

ጎትቶ ያመጣው መከራና ሥቃይ የነፍስን ጤንነት ከሚበካከለው፣

እንዲህ እንዲህ ጣቁሶ በሚያመጣው መዘዝ

በልዩ ደዌያት ሠውነቱ ሲያዝ

በሽታው ፀንቶበት አካሉ ሲመረዝ

እሱ ምንም አይሆን ተሠቃይዋ እያለች ያቺ የዋሂት

ነፍስ በተፈጥሮ ትዕዛዝ።

ምነው በዚህ ብቻ ታሪኩ መች ያልቃል

አለእንጅ መከራው ከሞትም በኋላ ሥጋ ባስከተለው ልዩ ልዩ

በደል መኮነን መቃጠል

በዝርክርክነት ሥጋ ሲኖር ባለም

በሠራቸው ግፎች እሱ አይጠየቅም።

ነፍስ ናት ኃላፊ ለሥጋዋ ወኪል

ሙሉ ነገረ ፈጅ ቀላጤ ለአካል።

እኔ እንደሠማሁት እንደሚባለውም

ፍርዱን ተቀብላ ወደ ደይን የምትሰጥም

የዋኋ ነፍስ ናት ሥጋ አይጋራትም

በመካነ ፍዳ በሲኦል ገሃነም

በሌለባት ጠባይ መቃጠሏ አይቀርም

ሥጋ ኃጥእ ሲሆን ሲኖር በዚህ ዓለም።

ስለዚህ ነው አሉ ሥጋን የምትመክር

በዚህ ዓለም ሳለ ከህግ ውጭ እንዳይኖር።

ትላለች ሁልጊዜ በመጠኑ በላ በመጠኑ ጠጣ

በቁንጣን በስካር መከራ ሲመጣ

ተካፋይ እንዳትሆን ከችግሩ ጣጣ።

ትመክራለች ሁሌ ትርፍ እቃ እንዳይኖረው

ድምር ህዝብ ሲነሳ ባካፋ እንዳይለው

እሷም እንዳትለፋ በዚያ በዘረፋው።

ትላለች ሁልጊዜ ለሠው ደግ ሥራ

አድሞ ሲነሳ እንዳታይ መከራ

እሷም እንዳትቀምስ ከስጋዋ ጋራ።

እንደመከረች ናት ዘወትር ዘላለም

ተንኮል እንዳያስብ እንዳይረብሽ ሰላም

ምናልባት ሲረሽን እንዳይደርሳት እሷም።

ታስጠነቅቃለች በሽታ እንዳይዘው

ሀኪም ቤት እንዲሄድ ሁሌ በየጊዜው

ታስጠነቅቃለች ሲጋራ እንዳያጨስ

በካንሰሩ ውጤት ኳላ እንዳትበጠስ።

ታስጠነቅቃለች አልኮል እንዳይጋት

ናላው ተበጥብጦ ህሊናው እንዳይስት።

እንደ መከረች ናት በውቀት እንዲበስል

ታውሮ እንዳይኖር በድንቁርና ኃይል።

ዛሬም እንኳን ቢሆን ሥጋ ቢያበሳጫት

ፊት ለፊት መምከሯን አልተወችም ብትሞት።

ከቶም አንዳንዴማ እንዲህ ትለዋለች

በዛች አነጋገር ስጋዋን ስትተች።

“ . . . እስክታገኝ ድረስ የስጋህን ዋጋ

በነፍስ አትጫወት ተውስጋ ተውስጋ ”

/ባለሌላው ጉልበት ምሱን እስኪሰጥህ

በነፍስ አትጫወት ተውስጋ ይቅርብህ

ከኮሬብ ከአዜብ በሠረፀው እሳት፣ በሠረፀው ነፍስ አማላጅ እንበልህ

ተዋህዶነቷን አትንፈጋት ለነፍስ ተው ስጋ ይቅርብህ

ባንተ የሚደርሰው ማናቸውም ችግር በኔ በነፍስህ ላይ እንደሚደርስ አውቀህ

ችግር ከሚፈጥሩ ጠንቃዊ ነገሮች ተቆጠብ እባክህ/

ልዩ ኃይል አግኝቶህ እስክታገኝ ዋጋ

በነፍስ አትጫወት ተው ስጋ ተው ስጋ።

ኋላ አንተ ስጋ መከራና ስቃይ ከሚያገላብጥህ

አሁን ባለህ ጊዜ በነፍስ ማሾፍ ምነው ቢቀርብህ ?

ጊዜን ጊዜ ገጭቶት እስኪሰጥህ ዋጋ

በነፍስ አትቀልድ ተው ስጋ ተው ስጋ።

መዋቲ ከህያው ረቂቅ ከግዙፍ ከቶ እንዴት ይጣላል ?

ግብዝ አንተ ስጋ ከነፍስ መጣላቱን ብትተው ይሻላል

ሥነ ፍጥረት እንኳ ለህያው ማድላቱን ብታውቅ ይበጅሃል።

ነፍስን መበደሉ ኧረ ተው ይቅርብህ

ተው ተለመን ሥጋ ስለ እግዜርህ ብለህ።

ሠላሳ አመት አለኝ እኔ ባንተ ስኖር

ነገር ግን ከችግር ከስቃይ በስተቀር

ያገኘሁት የለም ከቶ ቆራጣ ብር።

የምን ነፍሳዊ መብት የምንስ ነጻነት?

የምን ትክክል ፍርድ የምን ምኞት ድሎት

እኔ አላውቃቸውም በዚያ ባንተ ግዛት።

እንዳልናገርም በውስጥህ ታፍኜ

በየደረስኩበት ዲዳ ፍጡር ሆኜ

አፌ ተለጉሞ በዚያ ባንተ አካል

ሥጋ የበደልከኝ ስንቱ ይነገራል/

ለመማር ፈልጌ በነፍስነት ምግባር

ዕውቀት ካለበት ከጥበባት አድባር

ገብቼ ስቀስም የትምህርትን ማር

ታስቸግረኛለህ እኔን በማባረር።

ሥነ መለኮቱ ሰውሮህ ብትኖርም

ተው ስጋ ተጠንቀቅ ኋላ አታመልጥም

ከመቃብር ቤትህ ሄደህ ስትል ግድም።

መሬትና ውሃው ባህርይህ ቢነግሱ

በነፍስ አትቀልድ ተው ስጋ ስለነፍስ።

ሥጋን በሥጋ ነው ማጥቃቱ ቢባልም

ተው ሥጋ ይቅርብህ ነፍስም አትቦዝንም።

ልዩ ኃይል ተፈጥሮ እስኪያወልቅ መንጋጋ

በነፍስ አትጫወት ተው ስጋ ተው ስጋ።

እኔን እስካላወቅህ አንተ ብትደሰት

ከቶ ግድ የለኝም አይሠጠኝም ስሜት።

ስለዚህ ጨልጠው ፍሮግ ሱፑን ሾርባ

እንኳን በሆድ ቀርቶ በጀርባ እስኪገባ።

ሰልቅጥና ዋጠው የስፓኙን አሮስቶ

እስኪወጠር ድረስ ያ ቦርጭህ ተነፍቶ።

ቀምቅመው ውስኪውን የንግሊዙን ስኮች

ናላህ ጦዞ ጦዞ እስኪሆን ኮረኮንች።

መዘርዘር አያሻም ሁሉንም ኢጋብሰው

ግን እኔን አደራ ነፍሴን አታቃውሰው

ነኝና ወገንህ ግማሹ ላንተ ነው።

ልብስ ገበርዲኑን እንደፍላጎትህ

አካልን መሸፈን ደስታ ከሰጠህ።

ደርበው ከላይህ ሀሩን መንጦልያ

በልብስህ ቢያከብርህ ያ ወጣት ቡቃያ

ወይም ከቦህ ያለው ድፍንፍን ጆንያ

ከቶ እማይሻለው ከአሠር ፋንድያ።

ራስህን ታሸግ ሳራት ጣቃ ሱቲ

ወይም በራሱ ቁር እንደሞቶር ኩቲ

ወገብህን ታጠቅ በዝናር ኮረንቲ

ከድቶ እንዳይሸሽህ የከበበህ መልቲ።

የምትኖርበት ቤት በውበቱ ይቅበጥ

በወርቅና በአልማዝ ታጅሎ ይንቆጥቆጥ

ያንተን ግብዝነት እንዲሸፍንልህ ስትቀመጥ በውስጥ።

ለብሰህ ካባ ላንቃ ውጣ ካደባባይ

ለጅሎ እንድትመስለው የወረድክ ከሰማይ።

ተኮፈስ በኩታ በበርናስ ተከሸን

ደራርበህ ተላበስ አብደላ ከኒውን

ከጎፈር ጋር ለምዱን

ያንን ግምጃ ሱሪ ቅይር ልብ አልማውን

የተንቆጠቆጠ በወርቅ በካርካዴን

በነአንቆጳዝዮን

ምናለበት ቢረዳህ ለመምሠል ሠዎችን መማረክ ጅሎችን።

በጣትህ አስገባው የጣቱን ቀለበት

ባለ ሽ መህለቅ ኪሎውም ሀሞሳሶስት

ሰዎች ካልታዘቡህ ካላጣህም ጉልበት

ይረዳሃልና ግርማ ሞገስ ሆኖ ለማቅላት ሰውነት።

እንዲያ ተሸትረህ እንዲያ ተለብጠህ ብትመስል ጣኦት

በውጫዊው መምሠል ብታስንቅ መላዕክት

የሮም የአቴና ግማሽ እግዜሮችን ብታክል በውበት

ለእኔ ለነፍስህ ኢምንት ብናኝ ታህል አይሠጠኝም ስሜት።

በልብስ ተሸሞንሙነህ ህዝብን ብታጋድል

ያ ሁሉ ያንተ ጌጥ ለኔ ምንም አይደል።

እንዴት አይገባህም አንተ ግብዝ ሥጋ

አንተ ስለለበስክ እኔ አላገኝ ፀጋ

ያንተ ልብስ እኔ ዘንድ አይችልም ሊጠጋ።

እኔኮ ነፍስ ነኝ ግዝፈት አልባ መንፈስ

በረቂቅነቴ ያንተን ልብስ የማልለብስ።

ታዲያኮ ምንድን ነው ቅናትህ ፍርሃትህ

እኔን የምትጠላ አንተ በመልበስህ።

ቀየው ከዘመን ጋር አንድነት ተባብሮ እስኪሰጥህ ዋጋ

በነፍስ አትጫወት ተው ሥጋ ተው ሥጋ።

አንዳንዴ እስቃለሁ ሁኔታህ ሲታየኝ

የምትሆነው ሁሉ አላስችልህ ብሎኝ።

ትዋባለህ አሉ ወጣቱን ለመምሰል

ልብህ እያወቀው ዘመንህ እንዳይደል።

እኔ ምን ቸገረኝ ዐይንህን ብትኳል በእሸኮኮ ሀሞት

ጥርስህም ቢነቀስ ዓይነ ሥውር ድመት በምትሠጠው ወተት።

እኔ ምን ቸገረኝ ግምባርህ ቢነቀስ በአንበሳ ምራቅ

ጭንህም ቢነቀስ በዚያ ልዩ ከሠል በነጎድጓድ መብረቅ

ፊትህ ቢወለወል በዚያች ጥርኝ ላብ ያወዝህ እንዳይደርቅ።

እኔ ምን ጨነቀኝ እግሮችህ ቢታሹ በቀበሮ ሞራ

ከንፈርህ ቢቀባ ያንን ምናምንቴ ያርባሺ አሞራ።

እኔ ምን ተዳዬ ጠቅላላው አካልህ ለውበት ሲል ቢሞት

ሥጋህን ስታሸው ባገኘኸው ሁሉ ከንሥሣት ካራዊት።

እንድታውቅልኝ ግን እኔ ምፈልገው

ያንተን መዋብ መኳል ለኔ ለረቂቁ አለመጥቀሙን ነው።

ይጭር ይጭርና በሚያመጣው መዘዝ

ጤና እንደነሳኝ ነው እኔኑ ሲያስተክዝ።

ተበድሮ አምጥቶ በበላው እራሱ

ይህ ለነፍሴ ይሁን ስለማይል ከርሱ

ትርፍ ማሰብ ሆኗል ያገኘሁት ከሱ

ዕዳ ከፈል ሲባል ተካፋይ ነኝና በፈጠረው ጦሱ

እኔው በመሆኔ የሥጋዊ ነፍሱ።

እባክህ ፁም ስለው በጾም እየበላ

እኔን ነፍሱን ሳይሆን ሊጠቅም የርሱን ገላ።

ሊያስኮንነኝ ደርሷል ጀሃነም ሊያስገባኝ

እርሱ የሞተ-ለት ከእድሜው በኋላ በመቃብር ሲዋኝ።

እርሱ ለለበሰው ሱፍና ገበርዲን

እርሱ ለጨለጠው ሻምፓኝ ውስኪና ጅን

እርሱ ላጣጣመው ቅቅልና ፍትፍት ጥብስና ዶሮ ወጥ አትክልትና ጎመን

ለምንስ ልታማ ለምንስ ልኮነን

በኔነቴ ፀባይ በመንፈስነቴ እንደሆንኩ ስታመን

ከቶ የማልበላ ፍፁም የማልጠጣ መልበስም የማላውቅ ደግሞም የማልሰስን

እንዴት ከሥጋ ጋር ባንድ ተደምሬ ልቀጣ ልኮነን።

ድሮም ተብሎ አልቋል በነዘርዓያቆብ

ሥጋ እንደሆነ ላጠፉ መላዕክት መከተሪያ ግድብ

ታፍነው በስቃይ እንዳይኖሩ በደጉበ

ቤተሞቅህ ሆኖ ቅጣት የሚያዩበት በሥርአት በአግባብ

ደግሞም ላልቀመሠው ሊሆን ማስፈራሪያ መቀጣጫ ገደብ።

በአንበሳ ቆዳ የተሠራው ጫማህ

የሚሠጠው ጥቅም ለኔ አይምሠልህ

ተደስቶም እንደሁ ያ እግርህ ይንገርህ።

የሃገሬ በጎች በሚሠጡት ፀጉር

የተሠራው ልብስህ አንተን ቢያንቀባርር

ለኔ እንዳልጠቀመ ራሱ ይናገር።

የሃገሬ ጥርኝ የምትሠጠው ሽቶ

መዓዛ በመስጠት እንድትኖር አዝናንቶ

የረዳው አንተን ነው ለኔ አይደለም ከቶ።

ለምለሚቱ ሀገሬ በለምለምነቷ የምትሠጠው እህል

ጥቅሙ ያንተው ነው ያከርሣሙ ሆድህ ሁሌ እንዳይጎድል።

ሲሞላ ሲታፈስ ሲሞላ ሲታፈስ ዘወትር ሲታገል

ለኔ ምኔም አይደል ቢሞላ ባይሞላ ያንተ ግብዝ አካል

ዱሩ ሸንተረሩ ቢያበቅል ብዙ ዕፅዋት

ቆርጠህ ብትሠራበት ትልቁን አዳራሽ ሰማይ ጠቀሱን ቤት

አፈሩን ደልድለህ ተዝናና ብትለኝ በደረቅ ባዶ አንጀት

ታውቃለህ ስጋዬ በዚያ ነፍስነቱ እንደማልኖርበት

ያንተው እንደሆነ ታላላቁ ጥቅም የምታጓራበት በስጋነት ስሜት።

ለሆድህ እንደሆነ አምላክ ያዘጋጀው የጮመየው ሠንጋ

ሙክት ፍየሉ ዶሮው እንቁላሉ ጠቦቱ ቢንጋጋ

ላሟ የምትሠጠው ወተቱ አይቡ

ቅቤው ሆነ ሾርባው የሥጋዋ ድልቡ

ከቶ ለኔ አይጠቅምም ካሳቡ በስተቀር

ሥጋ ነህ ብቻህን ኮምኩመህ የጨረስክ ምናምን ሳታሴቀር።

እኔን ያስደነቀኝ ሌላ ሌላው ሳይሆን

ሸንኩርቱ ማኩራቱ ዛፉ ማቆጥቆጡ አበባው ማበቡ ምንም ሳይመርጥ ቀን

ላሚቷ መውለዷ ዶሮዋ መጣሷ ከቶም በጠቅላላ ተፈጥሮ

ማርገዷ ስትል አንተን አንተን

ይገርመኛል በርግጥ የተሠጠው እድል ባይጠፋ ባይባክን

ታዲያ ምን በወጣኝ ለምንስ ትታሠር ህያዋ ምላሴ

ተናግሬው ልረፍ በደልህን ሁሉ አልፈልግምና መታፈን በነፍሴ

ታዲያ ለምን ይሆን አንተ በበላኸው እኔ መጠበሴ።

ስለዚህ ጎራህን እኔም አሻፈረኝ

እንደበላህ ግፋ ዳፋህ አታድርገኝ . . .”

አለምና ሠዎች ባንድነት እስካሉ

እሊያ ሥጋና ነፍስ ናቸውም ነበሩ አሉ እንደተጣሉ።

ስለዚህ ወገኔ እኔ ምን አለፋኝ

መንታ ተቃራኒ ሁለት ተቃራኒ ተፋቅረው ላይኖሩ ሎሸኩ ሲታየኝ

ያቺ ነፍስ ለሥጋ ያ ስጋ ለዚያች ነፍስ ምንጊዜም ላይተኙ ስሪቱ ሲገባኝ

ኧረ ለምን ይሆን እኔን ያኣተተኝ ?

አንድ ቀን ተቋጭቶ ግዙፉ ቅራኔ አንድነት ላያገኝ።

በተዋህዶ ስምረት ሁለት አንድነቶች ዋህድ እስከሆኑ እስከዚያ ቀን ድረስ

እርቃነ ነፍስና ቁር ለበሱ ስጋ እስኪፋጭ እርስ በርስ

እኔም እንደሰዉ ገለልተኛኮ ነኝ ረቂቃዊት ነፍስ

ምንም የማልበላ ኩቶም የማልጠጣ ልብሶችን የማልለብስ።

ስለዚህ ሌሠቃይ ህይወቴ እስካለ ሞትን እስከንተራስ

መቃብሩ ገብቶ አካሌ እስኪፈርስ

ከዚህ የተለየ ሌላ ምርጫ የለም ብፈርጥም ብጠበስ

ይህንኑ ሆኜ ልቀጥል ኑሮዬን እስከሞኩኝ ድረስ

በሉ ደህና ሁኑ አደራ አትርሱኝ ምንጊዜም በመንፈስ

ሳታውቁኝ አትቀሩም እኔን ባይተዋሯን የስጋ ውስጥ ነፍስ

በሉ ደህና ሁኑ ስለ ነፍስ አትርሱኝ ምንጊዜም በመንፈስ።

በኃይሉ ገ/ዮሐንስ

1960 ዓ/ም